# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE FOURTEEN: ዕቅዱ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

## SCENE 1: ንጉሴ RETURNS HOME FROM SCHOOL

- ንጉሴ (M, 16)
- ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)

## SCENE 2: ሉሊት LEAVES አቶ ሙላቱ

- ሉሊት (F, 40)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)
- ምህረት (F, 15)

## SCENE 3: አቶ ጃለታ COMES HOME WITH TWO POLICE OFFICERS

- አቶ ጃለታ (M, 45)
- POLICE OFFICER 1 (M, ?)
- POLICE OFFICER 2 (M, ?)
- ንጉሴ (M, 16)
- ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 40)

## SCENE 4: ዳንኤል AND በለጠ PLAN TO SNEAK ምህረት INTO THE DORM

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **በለጠ (M, 15)**

### 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርብላችሁ ክፍል 14 ድራማ ነዉ። የዛሬው ርዕስ «ዕቅዱ»ይሰኛል። እስቲ ከመጀመራችን በፊት፤ ያለፈውን መለስ ብለን እናስታውስ።

ባለፈው ክፍል ዳንኤል ከምህረት ጋ በግልፅ ማውራት መፈለጉን ተረድተናል:

2. **ዳንኤል (EP 13, 65):** "ምህረት፤ አንድ ነገር ማወቅ ግን እፈልጋለሁ። እውነቱን ንገሪኝ። እኔ እንደምወድሽ ትወጂኛለሽ?
3. **ምህረት (LINE 73):** (…) አዎ! እወድሃለሁ ነገርኩህ አይደለል እንዴ?
4. **ዳንኤል:** እንግዳውስ አሳይኝ። እንደምትይው እውነትሽን ከሆነ አረጋግጪልኝ። **(& LINE 78)** በዚህ በሳምንቱ መጨረሻ ክፍሌ እንድትመጪ ጋብዤሻለሁ። ታድያ ብቻሽን እንደምትመጪ እርግጠኛ ሁኚ።

ምህረት ዳንኤል እንዳላት ትሄድ ይሆን? በሌላ በኩል ሌቦች ቤቱን ሰብረው ሲገቡ የንጉሴ እናት ብቻቸውን ነበሩ :

5. **ROBBER 1 (EP 13, 99):** ሲትዮ ፤ ጭጭ ብትይ ይሻልሻል። ሌላ አንድ ድምፅ አሰማለሁ ብትይ፤ ጉሮሮሽን ይዤ ሲጥ አደርግሻለሁ።
6. **SFX: MASKING TAPE BEING RIPPED**
7. **ROBBER 1 (LINE 105):** (…) አፍሽን ዝጊ መጮህሽን አቁሚ።

በመቀጠል ምን ይከሰት ይሆን? ንጉሴ ወደቤቱ እየሄደ ነው። ምህረት ዳንኤልን በመምረጧ እንዳዘነ ነው።

**<u>SCENE 1: ንጉሴ RETURNS HOME FROM SCHOOL</u>**

8. **SUBURB ATMO**
9. **SFX: FOOTSTEPS WALKING OUTSIDE**
10. **ንጉሴ:** **(talking to himself)** ምህረት ምንም የማይገባት የሆነች ደነዝ ነገር ናት። በአጠቃላይ ሴቶች ሲባሉ ደነዞች ናቸው! **(kicks a can)**
11. **SFX: CAN KICKED, SLIDES AWAY**
12. **ንጉሴ:** እማዬ ደግሞ ዛሬ ለምንድን ነው ልትወስደኝ ያልመጣችው? ሌላ ጊዜ ቢሆን ይሄኔ ስንት ሠዓት ላይ መጥታ ነበር ።ይገርማል። **(realizes something)** እረ ወይኔ ? በሩ ተበርግዷል። የእማ መኪናም የለችም።
13. **SFX: ንጉሴ'S FOOTSTEPS APPROACHING CAREFULLY**
14. **ንጉሴ:** **(shocked)** ወይኔ! የፊት ለፊቱ መስኮት ተሰብሯል። **(calls out in a panic)** እማዬ! አባዬ!
15. **SFX: FOOTSDTEPS LEAVE**
16. **SFX: DOOR CREAKING OPEN SLOWLY**
17. **SFX: FOOTSTEPS ON BROKEN GLASS**
18. **ንጉሴ:** **(utterly shocked)** በፍፁም! ይሄማ እውነት ሊሆን አይችልም። ተዘርፈናል ማለት ነው።
19. **SFX: FOOTSTEPS ON CARPET**
20. **SFX: WOMAN WHINES WITH MOUTH TAPED**
21. **ንጉሴ:** **(sees his mother)** በፈጣሪ። እማ ተርፈሻል? ደህና ነሽ?

22. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (tries to mumble some words with taped mouth)

23. ንጉሴ: ቆይኝ ቆይኝ። ፕላስተሩን ከአፍሽ ላይ ላንሳልኝ።

24. SFX: TAPE BEING RIPPED FROM MOUTH

25. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (screams in pain) ወይኔ!.... (cries uncontrollably)

26. ንጉሴ: እማ ደህና ነሽ? ምንድን ነው የሆነው?

27. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (sobs and sighs)

28. ንጉሴ: (scared voice) እማዬ። ነቃ ቀና በይ። መራመድ ትችያለሽ?

እባክሽ አንድ ነገር በይ። እያመመሽ ነው?

29. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (continues to cry) ሁሉንም ነገር ጠራርገው ወሰዱት።

30. ንጉሴ: እሺ ቆይኝ አንዴ። አባዬን ልጥራው።

31. SFX: FOOTSTEPS WALKING ON GLASS/CARPET

32. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (sobs in the background)

33. SFX: BEEP OF BUTTONS BEING PRESSED ON MOBILE PHONE, DIALLING

34. ንጉሴ: አባዬ ፤ ወደቤት መምጣት አለብህ። በጣም አስከፊ ነገር እቤታችን

ተከስቷል። ...

35. MUSIC INTERLUDE

## SCENE 2: ሉሊት LEAVES አቶ ሙላቱ

**36. DAYTIME ATMO, LIGHT TRAFFIC**

**37.** አቶ ሙላቱ: **(drunk voice all through this scene)** ሉሊት እስቲ ገምቺ? ተመልሼ ሀብታም ሆኛለሁ።**(laughs)** ተመልከች…ይህንን ን ሁሉ ገንዘብ።

**38. SFX: BUNDLE OF NOTES BEING SHUFFLED**

**39.** ሉሊት : ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም ሙላቱ። አድምጠኝ። ጥዬህ መሄዴ ነው።

**40.** አቶ ሙላቱ: እንዴ? እንደዚህ ሀብታም ስሆን ጥለሺኝ ልትሄጂ? ጅል አትሁኚ ሉሊት ።

**41.** ሉሊት : ባለትዳርና እናት ሆኜ የቻልኩትን ሁሉ ሳደርግ ቆይቻለሁ። ግን ይህ ሁላ ላንተ በቂ አይደለም። በቃኝ ሰለቸኝ። ወላጆቼ ቤት ተመልሼ  እገባለሁ።

**42.** አቶ ሙላቱ: እረ እንደውም ጥሩ ሀሳብ ነው። አባትሽ ሳገባሽ የከፈልኩትን ጥሎሽ በሙሉ ይመልሷታል። ከዛ በኋላ እንደውም የበለጠ የናጠጠ ሀብታም እሆናለሁ።…

**KW BEGIN**

**43.** ሉሊት : የምን ጥሎሽ ነው የምትለው ሙላቱ? እኔን ስታገባ ለአባቴ የሰጠኸው እኮ አንዲት ዶሮ እና ሁለት ፓኮ ክብሪት ነው።

**44.** አቶ ሙላቱ: ነው እንዴ? ዶሮ ቢሉሽ ዶሮ መሰለችሽ ፤ ያውም እንቁላል በትዕዛዝ የምትጥል ምርጥ ዶሮ እኮ ነች። **(laughs jokingly)**

**45.** ሉሊት : ቀልድህን መስማት አልችልም። ልታደምጠኝ ትችላለህ። እቃዬን ጠቅልያለሁ። ምህረትን ነው እየጠበኩ ያለሁት። እንደመጣች ጥርግ እንላለን።

**46.** አቶ ሙላቱ: (furious) ምን አልሽ? ሉሊት ፤ የማይረባ ሀሳብሽን ወዲያ በይ።የለም ምህረት የትም አትሄድም። ማን የሚያበስልልኝ መሰለሽ? አንቺ መሄድ ከፈለግሽ መንገዱን ጨርቅ ያርግልሽ። ምህረት ግን እዚህ ነው የምትቆየው የትም አትሄድም።

**47.** ሉሊት : ሙላቱ እስኪ አንዴ እንኳን ከራስህ ውጪ ለሌሎች ማሰብ ትችላለህ? (pained) ምህረት የተውክልኝ ብቸኛ ልጄ ነች። ለምን እድሏን ታበላሻለህ? ከእኔ ጋ ትሂድ ትምህርቷንም አታቋርጥም።

**48.** አቶ ሙላቱ: እኔጋ ብትቆይ ትምህርቷን ታቋርጣለች ያለሽ ማነው?

**49.** ሉሊት : ምክንያቱን ልንገርህ። በመጀመሪያ ነገር ትምህርት ቤት እንድትሄድ አትፈልግም። የምትፈልገው ነገር ቢኖር እርሷን መዳር እና ገንዘብ ማግኘት ነው።

**50.** አቶ ሙላቱ: (pretends to snore) ደክሞኛል። መተኛት እፈልጋለሁ። ለወላጆችሽ ሰላምታ አቅርቢልኝ። ምህረት ግን የትም አትሄድም።

**KW END**

**51.** ሉሊት : (bitterly) ሙላቱ አንድ ቀን ለዚህ ለምትሰራው ስራ ዋጋህን ታገኛለህ። ያኔ ግን ዳዴ እያልክ እንዳትመጣ። ገባህ። ደህና ሁን!።

**52. SFX: DOOR BEING OPENED**

**53. SFX: STEPS WALKING INSIDE**

**54.** ምህረት: (cheerfully) ታድያስ እማ፤ ታድያስ አባዬ

**SILENCE**

**55.** ምህረት: (puzzled) እማ ምን ላግዝሽ? እንደውም ስለ ቅዳሜ ለሁላታችሁም የምላችሁ ነገር አለኝ።

**56.** አቶ ሙላቱ: (calm but firmly) ምህረት… እዚህ ነው… የምትቆየው።

**57.** ምህረት: እእእ? ምንድን ነው የምታወሩት? ድሮስ የት መሄጃ አለኝ?

**58.** ሉሊት : ምህረት ለአባትሽ የሆነ የሚበላው ነገር ስሪለት። እኔ አሁን መሄድ አለብኝ።

**59.** ምህረት: እረ ቆይ እማ። በእውነት ለእንቺና ለአባዬ የምነግራችሁ ነገር አለኝ።

**60.** ሉሊት : ለአባትሽ ንገሪው። እኔ ግን አሁን መሄድ አለብኝ።

**61.** ምህረት: የት ነው የምትሄጅው?

**62.** አቶ ሙላቱ: በኋላ እናወራለን ምህረት። ተያት እናትሽ ትሂድ አሁን።

**63. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: አቶ ጃለታ COMES HOME WITH TWO POLICE OFFICERS</u>**

**64. ATMO INSIDE CAR**

**65. SFX: SIRENS, HEARD INSIDE CAR**

**KW BEGIN**

**66.** አቶ ጃለታ : (in panic) እነዚህ የማይገባቸው ሹፌሮች። ቆይ ግን የት የት ነው አሁን መንዳት የተማሩት? እንደቸኮልኩ አይገባቸውም! ቤተሰቤ ተዘርፏል! ለማመን የሚዳግት እኮ ነው።

**67. OFFICER 1**: እባክዎ ይረጋጉ። ትንሽ ነው የቀረን ለመድረስ።

**68.** አቶ ጃለታ : ትንሽ? ትንሽ? ምን እያሉ ነው መርማሪ ፖሊስ? ትራፊክ ከያዘን እንኳን እኮ ይኼው ግማሽ ሰዓት ሊሆነን ነው።

**69. OFFICER 1**: እባክዎን ቁጣዎን ይተው፤ ረጋ ይበሉ። ለእንደዚህ አይነት ጥሪ ስመልስ የመጀመሪያ ጊዜዬ አይደለም። በርግጥ ለነዳጅ ባይከፍሉ ኖሮ፤ ከዚህ የበለጠ ጊዜ ሊፈጅ ይችል ነበር።

**70.** አቶ ጃለታ : ልክ ነው። ደርሰናል። በሚቀጥለው መታጠፊያ ወደ ግራ ታጠፉ።

**KW END**

**71. SFX: CAR INDICATOR TICKS**

**72.** አቶ ጃለታ : **(screams out of adrenaline)** እዚያ ጋ! ቤቴ ያ ነው፤ መርማሪ መኮንን። ትልቁ እና ነጩ ቤት፤ ባለ ጥቁር በሩ። በሩ እንደተከፈተ ነው።

**73. OFFICER 1**: መልካም።አየሁት። በሉ አሁን ስራችንን እንስራበት።

**74. SFX: CAR SLOWS DOWN AND STOPS**

**75. CAR DOORS OPEN HURRIEDLY. FOOTSTEPS OF THREE PEOPLE RUNNING IN FROM CAR**

**76.** አቶ ጃለታ : **(shouting)** የንጉሴ እናት ! የንጉሴ እናት ! የትነው ያለሽው?

**77.** ንጉሴ: **(far away)** አባዬ! እዚህ፤ ኩሽና ነው ያለነው።

**78. SFX: SOMEONE WALKING OVER BROKEN GLASS IN A HURRY**

**79.** አቶ ጃለታ : ሁሉም ነገር ደህና ነው? በምችለው ፍጥነት እየበረርኩ ነው የመጣሁት።

**80.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(still sobbing but a bit calmer)**

81. **SFX: TWO PEOPLE WALKING OVER BROKEN GLASS**

**KW BEGIN**

82. **OFFICER 1:** **(whispers to second officer)** መኪናውን የነዳሁት እኔ የሆንኩ መስሎኝ ነበር።

83. **OFFICER 2:** ሚስቱን ለመማረክ ፈልጎ ነው።**(laughs sarcastically)**

84. **OFFICER 1:** **(commands)** አሁን የመቀለጃ ሰዓት አይደለም፤ መርማሪ። በቀጥታ ወደ ስራህ። ሌቦቹ ትተውት የሄዱት ለማስረጃ የሚሆን ነገር ካለ ፈልግ። ሴትየዋን አንዳንድ ጥያቄ ላቅርብላቸው።

85. **SFX: SOMEONE WALKING CAREFULLY OVER BROKEN GLASS**

**KW END**

86. **OFFICER 1**: **(clears throat)** ዳግም የተገናኘው ቤተሰብ መካከል በመግባቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ነገር ግን ጥቂት ጥያቄዎች መሰንዘር ይኖርብኛል እመቤት።

87. ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(softly)** ምንም አይደል። ምንድን ነው መጠየቅ የፈለኩት መኮንን?

88. **OFFICER 1**: ከሌቦቹ እንጀምር። ምን እንደሚመስሉ የሚያስታውሱት ነገር አለ?

89. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ዳንኤል AND በለጠ PLAN TO SNEAK ምህረት INTO THE DORM</u>**

90. **SFX: ACTION MOVIE BEING WATCHED ON COMPUTER**

91. በለጠ: **(making enthusiastic sounds while watching the**

**film)**

**92.** ዳንኤል: **(sighs and clicks on mouse to pause)** በለጠ ፤ አንድ ነገር ልጠይቅህ ፈልጌ ነበር።

**93.** በለጠ: አቦ! ባክህ። የማየው ፊልም እንዲህ ጡዘት ላይ በደረሰበት ሰዓት አይደለማ! ፊልሙን ልጨርስና እናወራለን። አቦ ባክህ። ላፕቶፑን አትዝጋው።

**94. SFX: LAPTOP BEING CLOSED**

**95.** በለጠ: **(clicks his tongue, annoyed)**

**96.** ዳንኤል: መጀመሪያ እንነጋገር። ፊልሙን ከዛ በኋላም ማየት እንችላለን።

**97.** በለጠ: **(frustrated)** በል እሺ። ስለምንድን ነው የምንነጋገረው?

**98.** ዳንኤል: እሺ። በደንብ አድምጠኝ። ምህረት ከትምህርት ቤት በኋላ ቅዳሜ ዕለት እንድትመጣ ነግሬያታለሁ።

**99.** በለጠ: **(applauds in pride)** ዋው። በጣም አሪፍ ማን! … ግን በነገራችን ላይ ፤ ሴቶች ወደ ወንዶች ዶርም መምጣት እንደማይችሉ ረሳኸው እንዴ?

**100.** ዳንኤል: እንደማይችሉ? አቦ ባክህ፤ ትቀልዳለህ? ትምህርት ቤት ፊልም ማየት የተከለከለ ነው። ግን ምን እያደረግን እንደሆነ ረሳኸው?

**101.** በለጠ: ግን ዳንኤል፤ በእዚህ የተነሳ ከትምህርት ቤት ሁሉ ልትባረር ትችላለህ። የምሬን ነው የምልህ። ለመሆኑ መግቢያው ላይ ያለውን ጠባቂ እንዴት አድርጋ ሸውዳ ነው የምትገባው?

**102.** ዳንኤል: ያ ያንተ ድርሻ ይሆናል።

**103.** በለጠ: **(shocked)** ኦ! ነው እንዴ? ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ።

**104.** ዳንኤል: እስቲ ተረጋጋ። ስለሁሉም ነገር አስቤበታለሁ። ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም።

**105.** በለጠ: ጥሩ። መፍትሄ ካለህ አሪፍ ነው። ነገር ግን እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ …

**106.** ዳንኤል: አዳምጠኝ። እንዴት እንደምታደርግ እነግርሃለሁ። ፊልሙን እንደጨረስክ ደግሞ የተወሰነች ገንዘብ አስጨብጥሀለሁ።

**107.** በለጠ: እስካሁን አቅድህ አሪፍ ይመስላል።

**108.** ዳንኤል: **(getting impatient)** ስማ! እሺ! የተወሰነ ገንዘብ እና ሲጋራ ጆባ እልሃለሁ።

**109.** በለጠ: እንደማላጨስ ታውቅ የለ…

**110.** ዳንኤል: ባክህ ላንተ አይደለም። በሩ ላይ ላለው ጠባቂ ነው። ያንን ትሸጉጥለት እና ቅዳሜ ምሽት እንግዳ እንዳለህ እና እንድትገባ እንዲፈቅድላት ትነግረዋለህ። ያንተ ድርሻ ይህ ብቻ ነው። አለቀ!

**111.** በለጠ: **(confused)** አለቀ?

**112.** ዳንኤል: አዎ! ማለቴ አንተን በተመለከተ። የቀረውን ለኔ ተወው።

## KW BEGIN

**113.** በለጠ: ግን ጠባቂው ገንዘቡን እና ሲጋራውን አልቀበልም ካለስ?

**114.** ዳንኤል: እንዴት ነው የማይቀበለው። ስማ ሲጋራው ጋ ያ እንዳይመስልህ የመጨረሻ ከባድ ማርክ ነው ያለው። በዛ ላይ ተደብቆ ሲያጨስ አይቼዋለሁ። ደግሞም ዘበኞች ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል።

**115.** በለጠ: እእእ... የመጨረሻ ሀይለኛ እቅድ ነው!እና ምህረትን ተቀብዬ አንተ ድረስ እንዳመጣልህ ነው የምትፈልገው?

**116.** ዳንኤል: ኖ! ትቀልዳለህ እንዴ? አንተ እዚህ ነገር ውስጥ እንዳለህ ማወቅ የለባትም። ዘበኛው ራሱ ይዟት ይመጣል። ያኔ ማንም አይጠረጥርም።

**KW END**

**117.** በለጠ: **(applauds)** ሀ ሀሀ... ከዘመኑ ሞባይል የበለጠ ስማርት ነህ።

**118.** ዳንኤል: ቀልድህን አቁም ባህክ በለጠ! የጠየኩህን ታደርግልኛለህ?

**119.** በለጠ: ምን ምርጫ አለኝ አለቃ? ግን ማለቴ በጣም አሪፍ፤ በል አሁን የጀመርኩትብ ፊልሜን ላጣጥም

**120.** ዳንኤል: **(groans)**

**121. SFX: ACTION MOVIE SOUNDS**

**122. CROSSFADE MUSIC THEME INTERLUDE**

**123. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

በዚሁ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ በሚል ርዕስ የሚቀርበውን የበማድመጥ መማር ድራማ ለዛሬ እናጠናቅቃለን። ዕቅዱ ተወጥኗል ግን ይሰራ ይሆን? የንጉሴ አባት አቶ ጃለታስ ሌቦቹ ማን እንደሆኑ ይደርሱበት ይሆን? በሌላ የጭውውቱ ክፍል እንመለስበታለን። ይህንን እና ሌሎች ክፍሎችን ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ዝግጅት ድረስ ጤና ይስጥልን።